Washington State Parks

EMBRACE YOUR NATURE

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ምን ፓርኮች፣ የመዝናኛ ስፍራዎች ክፍት ናቸው?**
ጁን 4፣ አብዛኛዎቹ የመንግስት ስፍራዎች ለ **እለታዊ-ጥቅም**ክፍት ናቸው።

**ካምፒንግ** ብዙ ሀገራት ውስጥ እየተከፈተ ሲሆን በብዙ ወረዳዎች ውስጥ ደግሞ ወደ ደረጃ ሁለት ተንቀሳቅሰዋል። Jay Inslee Safe Start እቅድ።

በመንግስት የሚተዳደሩ የጀልባ ማስፈንጠሪያዎች እና ማሪናዎች በክልል ፓርኮች ጀረጃ 2 ወረዳ ውስጥም ክፍት ናቸው።

አሁን ያሉትን የካምፕ ስፍራዎች፣ ፓርኮች እና ሌሎች በክልል የሚተዳደሩ የመዝናናኛ ስፍራዎች የሚከተሉትን ይጎብኙ:

- Washington State Parks — የፓርክ ሁኔታዎች
- Washington Department of Fish and Wildlife — የተዘጉ ስፍራዎች ዝርዝር እና ገደቦች
- Washington State Department of Natural Resources — ክፍት የሆኑ መዝናኛዎች

**ያስታውሱ:** አንዳንድ በ ደረጃ 2 ውስጥ ያሉ ወረዳዎች ለካምፒንግ፣ ወዲያውኑ **ክፍት ላይሆኑ የሚችሉ ሲሆን** ይህም በወረዳው ባለስልጣናት በሚሰጥ መመሪያ መሰረት ነው። Washington State Parks እነዚህን ማህበረሰቦች የሚደግፍ እና አብሮሯቸው መስራት የሚቀጥል ሲሆን ካምፖችች መልሶ ለመክፈት ምርጠ የሆነው መንገድ የትኛው ነው የሚለውን ለማወቅ ነው።

**Discover Pass ያስፈልገኛል?**
አዎ። የ Discover Pass መኪናዎትን በWashington State Parks ኣማርኛ Department of Natural Resources (DNR) ክልል በሚተዳደር መዝናኛ ስፍራ እና ውሀ መድረስ ቦታዎች ለማቆም ያስፈልጋል። እነዚህ ስፍራዎች የክልል ፓርኮችን፣ የውሀ መድረስ ነጥቦችን፣ የታሪክ ስፍራዎች፣ የዱር እንስሳትን፣ DNR ካምፕ ማድረጊያ ስፍራዎችን፣ ትሬይሎችን፣ የትሬይል ጫፎችን እና በ DNR-የሚተዳደሩ መሬቶችን የሚያካትት ነው። የ Discover Pass የሚያስፈልገው ለእለታዊ ጥቅም ጉብኝት ብቻ ነው።

የ Discover Pass በተጨማሪም በ Washington Department of Fish and Wildlife (WDFW) በሚተዳደሩ መሬቶች ላይም ያስፈልጋል። ይህም ውሀ ጋር መድረስን እና የዱር እንስሳት ስፍራዎችን የሚያካትት ሲሆን፣ ይህም Vehicle Access Pass በትክክለኛ የአደን ወይም አሳ ማጥመድ ፈቃድ ግዢ ካለዎ ግን አያስፈልግም።

**ስፍራዎች ዝግ ለሆኑበት ጊዜ ለ Discover Pass ገንዘብ ተመላሽወይም ማራዘሚያ ማግኘት እችላለሁ?**
ለ Discover Passes ገንዘብ ተመላሽ ወይም ማራዘሚያ አናደርግም።

አመታዊው የ Discover Pass $30 ያስወጣል። የእለታዊ መግቢያ $10 ሲሆን አመታዊው መግቢያ በሶስት ጉብኝቶች ብቻ ለራሱ ይከፍላል።

በ 12 ወራት ሲካፈል ወርሀዊ ወጪው $2.50 ነው። የክልል ስፍራዎች ከ ማርች 23 እስከ ሜይ 5 ለአምስት ሳምንታት ዝግ ነበሩ።

በዚህ ጸደይ የመንግስ ስፍራዎች ክፍተኛ የሆነ የገቢ መቀነስ ኢጋጥሟቸዋል — ይህም በምጣኔ ሀብት መቀዛቀዝ ላይ ተጨምሮ ነው።

ነገር ግን፣ Washington state parks እና የክልል ስራዎች በዚህ ክረምት በተቻለዎ መጠን እንዲደሰቱባቸው የምንመክሮ ሲሆን ይህም ከማለፊያዎ ከሚያገኙት ትልቅ የሆነ ዋጋ በተጨማሪ ነው።

**መጫወቻ ስፍራዎች ክፍት ናቸው?**
የክልል መጫወቻ ስፍራዎች ማስታወቂያ እስከሚነገር ድረስ ዝግ ሆነው የሚቆዩ ሲሆን ይህም የ COVID-19 ተጋላጭነትን ለመቀነስ ነው።

**ሽንት ቤቶች ክፍት ይሆናሉ?**
አዎ። ክፍት በሆኑ ፓርኮች ውስጥ ሽንትቤቶች ክፍት በሆነባቸው የጥቅም ስፍራዎች የሚኖሩ ሲሆን የካምፕ ስፍራዎች ክፍት በሆኑባቸውም ስፍራዎች ይገኛል። ሽንትቤቶች በአንዳንድ ስፍራዎች እና ዝግ በሆኑ ስፍራዎች ላይ ዝግ ሊሆኑ ይችላሉ።

ዝግጁ ይሁኑ። የራስዎን የግል መከላከያ እቃ፣ ውሀ፣ ሳሙና፣ የእጅ ሳኒታይዘር እና ሽንትቤት ወረቀት እና ማንኛውንም ይዘው የሚመጡትን ነገር ይዘው መመለስ አለብዎ።

የፓርክ ቢሮዎች አሁንም ለማህበረሰቡ ዝግ ሲሆኑ፣ የጎብኚ ማእከሎች እና የፓርክ ህንጻዎችም ይካተታሉ።

**የውሀ ዳርቻዎች፣ የጀልባ ማቆሚያዎች እና ማሪን ስፍራዎች ክፍት ይሆናሉ?**
የውሀ ዳርቻዎች የሚፈቀዱ ሲሆን የጀልባ ማቆሚያዎች ክፍት በሆኑ ፓርኮች ውስጥ ይፈቀዳሉ። የውሀ ዳርቻዎችን የሚጠቀሙ ሰዎች አካላዊ መራራቅን ቤታቸው ውስጥ ከማይኖሩ ሰዎች አንጻር መለማመድ አለባቸው።

Marine የመንግስት ፓርክ ሽንትቤቶች ውስን በሆነ መጠን ይከከፈታሉ። ቆሻሻዎትን እባክዎ ያውጡ እንዲሁም በደሴቶች ላይ የሚጠጣ ውሀ አያገኙ።

**መልህቅ መጣል ቁጥጥር ወይም ክትትል ይደረግበታል? የባህር ዳርቻ ስፍራ ማቆሚያ ስፍራዎችስ?**
መልህቅ መጣል ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግበት ሲሆን ከ COVID-19 መዘጋቶች በፊት ቁጥጥር እንደሚረግበት ነው። ልዩ የሆኑ መመሪያዎች የሉም።

**መምጠጫዎች ክፍት እና በስራ ላይ ናቸው?**
በስቴት ፓርክ ውስጥ ያሉት ጥቂት መምጠጫዎች ክፍት ናቸው።

አብዛኛዎቹ ዋሺንግተን ውስጥ ያሉ መምጠጫዎች በመንግስት ወይም በ ህዝብ ማሪናዎች ውስጥ ናቸው። ጀልበኞች ማሪናዎች ክፍት መሆናቸውን እና መምጠጫዎች ደግሞ እየሰሩ ከሆነ ማረጋገጥ አለባቸው። ለዋሺንግተን ፓምፕአውት ቦታዎች: parks.state.wa.us/657/Pumpout ይጎብኙ

**አንድ ፓርክ ለአንድ ቀን ውሎ ብቻ ክፍት የሚሆን ከሆነ፣ ፓርኩ የሚዘጋው መቼ ነው?**
የአንድ ቀን ውሎ ፓርኮች ጸሀይ ስትጠልቅ ይዘጋሉ።

**ለካምፒንግ ሙሉ የገንዘብ ተመላሽ ወይም ለምሽት ጊዜ ቆይታ አገኛለሁ?**
ይህ የሚወሰነው በሚከተሉት ላይ ነው...

- **የምሽት ጊዜ ጎብኚዎች በዝጊዎች ተጽእኖ ውስጥ ይገባሉ:** የምሽት ጊዜ ጎብኚዎች በዝግ ምክንያት ተጽእኖ ደርሶባቸው ከሆነ ሙሉ የሆነ የገንዘብ ተመላሽ እናደርጋላቸዋለን።
- **ክፍት ወደሆኑ የካምፒንግ ፓርክ የሚመጡ ጎብኚዎች** ሙሉ የገንዘብ ተመላሽ ለምሽት ጊዜ ቆይታቸው የሚያገኙ ሲሆን፣ ይህ ግን የገንዘብ ዝውውር ክፍያዎችን አያካትትም ($8 እስከ $10 የቦታ ማስያዣ ክፍያ እና ከ $8 እስከ 10 የስረዛ ክፍያ)። ኦንላይን ከሆነ የቦታ ማስያዣውክፍያ $8 ሲሆን በስልክ ከሆነ ደግሞ $10 ነው።

አሁን ስላለዎ የካምፒንግ ቦታ ማስያዝ አገልግሎት ጥያቄ ያለዎ ከሆነ እባክዎ ለ (888) CAMPOUT ወይም (888) 226-7688 ይደውሉ።

**በአሁን ሰአት ዝግ በሆነ የካምፒንግ ፓርክ ውስጥ ቦታ አስየዤ ከሆነስ? ቦታ ማስያዜ ተሰርዞ ከሆነ የማውቀው እንዴት ነው?**
ከዚህ እየተለወጠ ካለ ሁኔታ ጋር ስንኄድ ስለሚያሳዩት ትእግስት እናመሰግናለን። የእረፍት ጊዜ እቅድዎን ለእርሶ አስፈላጊ እንደሆነ የምናውቅ ሲሆን እርሶ በሚወዱት የዋሺንግተን ካምፕ ማድረጊያ ስፍራ በዚህ የክረምት ጊዜ ካምፕ ማድረግ እንደሚችሉ ተስፋ እናደርጋለን።

በዚህ ምክንያት እርሶ ቀጠሮ ባስያዙበት ጊዜ ፓርኩ በእርግጠኛነት ዝግ እንደሚሆን እስከምናውቅ ድረስ ያስያዙትን ቀጠሮ አንሰርዝብዎትም። ስለዚህ፣ የታቀደው ቀንዎ እስከሚቀርብ ድረስ ከእኛ ምንም አይነት መረጃ ላይደርሶ ይችላል።

ለ ካምፒንግ ዝግ በሆነ ቦታ ላይ የተደረገን ቦታ ማስያዞችን ለመሰረዝ የምንፈልግ ከሆነ በኢሜይል ይህንኑ አሳውቀንዎት ሙሉ የሆነውን ገንዘብ ተመላሽ የምናደርግልዎ ይሆናል።

ከቦታ ማስያዝዎ ጋር በተያያዘ ምንም አይነት ጥያቄ ያለዎ ከሆነ፣ የቀጠሮ ማስያዝ ቡድናችንን በ 888-CAMPOUT (888-226-7688) ላይ ደውለው ያግኙ።

**የመንግስት መሬቶች የመጨናነቅ ጉዳይ ያለ ሆነ ይዘጋሉ?**
ቦታዎችን እንደገና ስንከፍት፣ ሰዎች ማህበራዊ መራራቅን እንዲተገብሩ እንጠይቃለን። ሰዎች በብዛት ሲሰበሰቡ ካየን ወይም ማህበራዊ መራራቅን የማይተገብሩ ከሆነ፣ ሙሉ ፓርኩን ወይም አንዳንድ ፓርኩ ጋር ያሉ ስፍራዎችን ልንዘጋ እንችላለን።

አዳዲስ ከ COVID-19 ጋር ግንኙነት ያላቸው ስጋት መከላከያ ጉዳዮች የሚመጡ ከሆነ፣ የ Washington Departments of Fish and Wildlife (WDFW) እና Natural Resources (DNR) እና State Parks ውስን በሆነ ማሳወቂያ ስፍራዎችን ሊዘጋ እና የማህበረሰብ ጤንነትን ሊያስጠብቅ ይችላል።

**ማንኛውንም የ መጨናነቅ፣ ቆሻሻ ወይም ሌሎች ስጋቶች ወይም ከዱር እንስሳት ጋር ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች ወይም ጀልባ ማስፈንጠሪያዎች ለ WDFW እንዴት ማሳወቅ እችላለሁ?**
ሰዎች በ Washington Department of Fish and Wildlife ድረገጽ ላይ ጉዳዮችን ማሳወቅ ይችላሉ ።

**አካባቢያዎ የክልል ፓርክ ለማጽዳት በጎ ፈቃደኛ መሆን እችላለሁ?**
በአሁን ሰአት አይችሉም። በጎፈቃደኞቻችንን እና ጠንካራ የሆነ ስራቸውን እናደንቃለን። ነገር ግን፣ ማስታወቂያ እስከሚነገር ድረስ ምንም አይነት የበጎ ፈቃድ ስራ አይሰራም። የ State Parks ካምፖችን መልሶ ለመክፈት እና ሌሎች የበጎ ፈቃድ ስራዎችን በዚህ ክረምት ጊዜ ለመስራት ስራ በመስራት ላይ ይገኛል። አዳዲስ መረጃዎችን ይከታተሉ ወይም የበጎ ፈቃደኞች ፕሮግራምን በ ያግኙ ወይም ለ (360) 902-8583 ይደውሉ።

**ካቢኖች እና ዩርቶች የሚከፈቱት መቼ ነው?**
ካቢኖች፣ ዩርቶች እና መጠለያዎች ዝግ ሆነው የሚቆዩ ሲሆን ይህም እስከ ጁን 30 ድረስ ነው። ካቢኖች ጁን ላይ መልሰው እንዲከፈቱ፣ አሁን ያሉ ክፍት ቦታዎች ይከበራሉ።

**የቡድን ካምፕ ማድረጊያዎች ክፍት ናቸው?**
የቡድን ካምፖች ማስታወቂያ እስከሚነገር ድረስ ዝግ ናቸው።

**የእረፍት ጊዜ ቤቶች ዝግ ናቸው?**
የእረፍት ጊዜ ቤቶች ማስታወቂያ እስከሚነገር ድረስ ዝግ ናቸው።